# የእውነታ ሉህ ቁ. ፰

# የዘር ልዩነት ድህነት ጦስ በኢሚግሬሽንና በአዲስ መጤዎች ሰፈራ


## ስደተኞች በስውር ዘዴ እንዴት ተጎድተዋል?

**መታሰር**: ካናዳ በኢሚግሬሽን መታሰር ጉዳይ ላይ ከፍተኛውን የጊዜ ገደብ በመጣል አታስገድድም
በከፍተኛ የፀጥታ እስር ቤት ውስጥ ለሰባት ዓመታት (ለብቻው ታጉሮ የቆየበትን 103 ተከታታይ ቀናት ጨምሮ) ታስሮ ሲማቅቅ የነበረውን አንድ ምዕራብ አፍሪቃ የኢሚግሬሽን እስረኛ እ.ኤ.አ በ2017 የኦንታሪዮ ከፍተኛ ፍርድ ቤት እንዲለቀቅ አዝዟል።

በዘር የተለዩ ከሰሜን አሜሪካ / ከአውሮፓ ውጭ ካሉ አገራት በወሲባዊ ዝንባሌ ወይም በጾታዊ መለያ ማንነት ምክንያት የሚሰደዱ ጥገኝነት ፈላጊዎች እንዲቀበልዋቸው ሲያመለክቱ በአሰራር ሂደት ውስጥ አሉታዊ ተጽዕኖ ይደርስባቸዋል።

የLGBTQ2S + አመልካቾችን የሚወክሉ ጠበቆች ደንበኞቻቸው ችሎት በሚቀርቡበት ጊዜ ስለ ወሲባዊ ልምምዶቻቸው ቀጥተኛ ምስሌያዊ እና ጣልቃ ገብ ጥያቄዎችን የሚጠየቁባቸው አጋጣሚዎች እንዳሉ ሪፖርት አድርገዋል።

ደግሞም እንደዚህ ዓይነት የመሳሰሉ ጉዳቶች በቂ የትርጉም አገልግሎቶችን ባለማግኘት በተደጋጋሚ እየተባባሱ ናቸው።



**የሰፈራ አገልግሎቶች**: ስደተኛ አመልካቾች፣ ስደተኛ ሠራተኞች እና ያልተመዘገቡ ስደተኞች በድህነት ውስጥ ከመጠን በላይ የተወከሉ ናቸው።
እንዲሁም የቋንቋ ስልጠናን ጨምሮ በፌደራል ለሚደጎሙ የሰፈራ አገልግሎቶች ብቁ አይደሉም።
ብዙውን ጊዜ እንደዚህ ዓይነት ያሉ ድጋፎች በጣም የሚያስፈልጓቸው ናቸው።
**የካናዳ የሕጻናት ጥቅማ ጥቅም** (CCB): በማያስተማምን የስደተኝነት ሁኔታ ያሉ ወላጆች ለድህነት ቅነሳ ልኬት ተብሎ ተግባር ላይ ከዋለው የካናዳ የሕፃናት ጥቅማ-ጥቅም አገልግሎት የተገለሉ ናቸው።
በካናዳ ውስጥ በዚህ ችግር ከሚገኙ ወላጆች የሚወለዱ ሕፃናት እንኳ ወደዚህ የካናዳ የሕጻናት ጥቅማ-ጥቅም (CCB) እንዳይገቡ ይከለከላሉ።

**ቤተሰብ፡** ቤተሰብ እንደገና እንዳይገናኝ፤ ወንድማማቾች / እህትማማቾች እንዲሁም የቅርብ ቤተ-ዘመድ የተባሉትን በሚለይ የኢሚግሬሽን ህግ ብዙዎች እንዳይገቡ ይከለከላሉ።

ስደተኛ ልጆችም ወላጆቻቸውን ወይም እህቶችና ወንድሞቻቸውን ስፖንሰር አድርገው ማምጣት አይችሉም፤
እንዲሁም ከ ኤል አይ ሲ ኦ (LICO) በታች ወይም በማህበራዊ ድጎማ ላይ የሚኖሩት ስፖንሰር ለማድረግ ብቁ አይደሉም ።

**ቋንቋ፡** እንደ ጤና እና መኖሪያ ቤት ያሉ መሠረታዊ አገልግሎቶችን እንኳን ለማግኘት የቃል እና የጽሑፍ ትርጉም አገልግሎቶች አይገኙም፣ አገልግሎቶቹ የተገደቡ ናቸው።

የገንዘብ አቅማቸው ውስን የሆኑት ሰዎች ለቋንቋ ትርጉም ምስጢራዊ ወይም ስሜታዊ በሆኑ ጉዳዮች እና ሁኔታዎች እንኳ ሳይቀር ብዙውን ጊዜ በልጆች፣ በቤተሰብ፣ በጓደኞች ወይም በሚያውቋቸው ሰዎች  ይተማመናሉ።

**የኢኮኖሚ ስደተኞች** ማለት በችሎታ ወይም በትምህርት ምክንያት ወደ ካናዳ መጥተው ተቀባይነት ያገኙ ሰራተኞች እና ቤተሰቦቻቸው ናቸው ።

**የቤተሰብ ክፍል ስደተኞች** ማለት በካናዳ በሚኖር አንድ የቤተሰብ አባል ምክንያት ስፖንሰር ሆነው የሚመጡ ሰዎች ናቸው።

**ኮንቬንሽን ስደተኞች** ማለት በሌላ አገር ስደት ያጋጠማቸው በመሆኑ በካናዳ ጥበቃ የተሰጣቸው ሰዎች ናቸው።

**ስደተኛ አመልካቾች** ማለት በካናዳ ውስጥ ያሉ እና ለጥበቃ ጥያቄ ያቀረቡ ሰዎች ናቸው፤ ሆኖም ከግማሽ በላይ የሚሆኑ የይገባኛል ጥያቄዎች ውድቅ ይደረጋሉ።

“**ስታትስ-አልባ**”፤ “**ያልተመዘገበ**” ወይም “**መደበኛ ያልሆነ**” የሚለው አባባል በካናዳ የሚኖሩትን፣ ነገርግን በተለያዩ ምክንያቶች ሕጋዊ ተቀባይነትን ሊያገኙ የማይችሉትን ማናቸውም ሰዎች ያመለክታል፣ ወይም ህጋዊ የነዋሪነት ስታተስ የነበራቸው ጊዜው አልፎ የተቃጠለባቸው ናቸው።

**እንደገና ማቋቋም** [Regularization] ማለት ስታተስ-አልባ፣ ያልተመዘገቡ ወይም መደበኛ ህጋዊነት ባለው ሁኔታ የሚገኙ ግለሰቦች በካናዳ ውስጥ ህጋዊ ስታተስ ለማግኘት እንደገና የማመልከት እድል የሚሰጣቸው ናቸው።

Colour of Poverty | Colour of Change

March 2019
www.colourofpoverty.ca

እ.ኤ.አ. በ2011 በካናዳ የሥራ መቅጥር አሰራር ላይ የተደረገው የኦዲት ጥናት እንዳሚያመለከተው የኤስያውያን ስም ያላቸው እና በውጭ ትምህርት የተማሩ ነገር ግን ሁሉም የካናዳ የሥራ ልምድ ያላቸው የሥራ አመልካቾች ስማቸው ከእንግሊዝ ከሆኑቱ ተመሳሳይ አመልካቾች ጋር ሲነጻጸሩ ለሥራ ቃለ-መጠይቅ የመጠራት ዕድላቸው 30% ያህል ያነሰ ነው።
የካናዳ እና የውጭ ድብልቅ የሥራ ልምምድ ካላቸው የመጠራት ዕድላቸው ከ46% በታች ያነሰ ነው፤ እንዲሁም ዓለም-አቀፍ ተሞክሮ ካላቸው የመጠራት ዕድላቸው ከ62% በታች ያነሰ ነው።

**መረጃ**: የካናዳ የድንበር አገልግሎቶች ኤጀንሲ በዘር፣ በጎሳ፣ በእምነት / በመንፈሳዊነት ወይም በትውልድ ሀገር የተከፋፈለ የእስር ዘገባ ስታቲስቲክስ አያሳትምም።

**ትናንሽ ልጆች፡** የካናዳ የድንበር አገልግሎት ኤጄንሲ (CBSA) ባቀረበው መረጃ መሠረት እ.ኤ.አ. በ 2016/2017 ውስጥ 151 ታናናሾችን/ሕጻናትን ጨምሮ 6,251 ሰዎች በኢሚግሬሽን እስርቤት ተይዘዋል።

**የሥራ ቅጥር ኢንሹራንስ** (Employment Insurance): እ.ኤ.አ. በ2012 በነበረው የወግ አጥባቂ መንግሥት በፕሮግራሙ ላይ የተደረጉት ለውጦች በትላልቅ የከተማ ማእከላት የሚኖሩ ሰዎች ብቁነት በከፍተኛ ደረጃ ቀንሷል። ይህ ሁኔታ በተለይ በቀለም ስደተኞች ላይ ያልተመጣጠነ ጉዳት አስከትሎአል።



## ፈጣን ማስታወሻዎች

ስለ ባለ ቀለም ህዝቦች ስንነጋገር የዘር መሠረታችውና ቅሬተ-ቅርሳቸው ከአውሮፓ ያልሆኑትን ካናዳውያንን ማለታችን ነው። እነዚህም ካናዳ ውስጥ የተወለዱና ከካናዳ ውጭ የትም የተወለዱ፣ በሁለቱም ጎራ ስላሉ የቀለም ሰዎች መናገራችን ነው።
ነባር የአገሬው ተወላጆች ስንል በአገሪቱ የነበሩ ቀድምት ህዝቦች {First Nations / Natives} [የተመዘገቡና እውቅና የተሰጣቸው እንዲሁም ያልተመዘገቡ) ሜቲስ እና ኢንዩት ስለሚባሉ ሕዝቦች ነው።
በቶሮንቶ ውስጥ በድህነት ከሚኖሩት ሰዎች ውስጥ 62% የሚሆኑቱ በዘር ልዩነት ከሚታዩ ቡድኖች የመጡ ናቸው። በካናዳም በዘር ልዩነት ከሚታዩት ውስጥ 52% የሚኖሩት በኦንታሪዮ ውስጥ ነው።

በካናዳ ውስጥ በዝቅተኛ ገቢ ተቆራጭ (LICO) ወይም በዝቅተኛ የገቢ ልኬት (LIM) የሚመደቡ ቤተሰቦች ከገቢዎቻቸው ውስጥ በጣም ከመቶኛ ውስጥ ትልቁን የሚያጠፉት በአስፈላጊና መሠረታዊ ነገሮች ማለትም እንደ ምግብ እና መጠለያ የመሳሰሉት ናቸው። ድህነትን የምንለካውም በዚህ መንገድ ነው።
**ስልታዊ ዘረኝነት** ብዙዉን በስውር በሚሠራ ተቋማዊና የተዛባ ፖሊሲ፣ ልምምድና አሠራር ምክንያት የሚፈጸም ሆኖ በተለያዩ ቡድኖች መካከል አንዱን ጠቅሞ ሌላውን የሚጎዳ አሠራር ነው።
የተወሰኑ ቡድኖችን በተለያዩ መንገዶች እንዴት ሊጎዳ እንደሚችል አስቀድሞ ግምት ውስጥ ያላስገባ፣ ሁልጊዜም እንደተለመደው አካሄድ ብቻ የመከተል ውጤት ሊሆን ይችላል።

**ለብዙዎች ህጋዊ እውቅናንና ተቀባይነትን በማይሰጥ እና አግባብ በሌለው የኢሚግሬሽንና የስደተኞች ህግ ምክንያት በዝቅተኛ ደመወዝ የተቀጠሩ ስደተኛ ሠራተኞችን ጨምሮ የ “ስታተስ-አልባ” ሰዎች ቁጥር ብዙ እየጨመረ ይገኛል።**

**ያለ ስታተስ የሆን እና እና ምንም እንኳ ግብር የሚከፍሉ ቢሆኑም በሕጋዊ መንገድ መሥራት አይችሉም እና ለጉዳት የመዳረግ እንዲሁም ለመበዝበዝ አደጋ የተጋለጡ ናቸው።**

**ከአገር እባረራለሁ በሚል ፍርሃት የፖሊስ ጥበቃንና እርዳታን መጠየቅ አይችሉም። ስለሆነም ለብዙ ፕሮግራሞችና እና አገልግሎቶች የተደራሽነት ዕድል ሊያገኙ አይችሉም።**

# ምን እየተደረገ ነው?

የካናዳ የስደተኞች ጉዳይ ምክር ቤት (CCR) በካናዳ እና በዓለም ዙሪያ ላሉት ስደተኞች፤ እንዲሁም በካናዳ ውስጥ የሚኖሩ ስደተኞች እና አዲስ መጤ ሰፋሪዎች መብቶቻቸውን ለማስጠበቅና ለማስከበር የቆመ የበጎ አድራጎት ጃንጥላ ድርጅት ነው።
www.ccrweb.ca / info@ccrweb.ca

OCASI - ለስደተኞች አገልግሎቶችን የሚሰጡ ኤጀንሲዎች ምክር ቤት በኦንታሪዮ፡
በኦንታሪዮ ውስጥ ለስደተኞችና አዲስ መጤ ሰፋሪዎች አገልግሎት የሚሰጡ ኤጀንሲዎች የጋራ ድምጽ የሆነ ጃንጥላ ድርጅት ሲሆን ለአንድ ክፍል (sector) እና ለሚያገለግሉ ግለሰቦች እና ማህበረሰቦች ተደራሽነትን እና ፍትሃዊነትን ለማረጋገጥ የሚሟገት ድርጅት ነው።
www.ocasi.org / generalmail@ocasi.org